ደጃዝማች አባይ ካሣ፤ ፊታውራሪ መሀመድ ዓሊ

እና

የአርሲ-ሮቤ ነዋሪዎች አመፅ፤

አሰግድ አረጋ ( ኮለምበስ-ኦሃዮ)

የሮቤ ነዋሪዎች የትግራዩን ልጅ የደጃች አባይ ካሣን የስብሰባ ጥሪ እረግጠው ወጥተዋል፤ ባለመደመጣቸው። አባይ ካሣም ተሳድበው ወደ መጡበት ባሽከሮቻቸው ታጅበው ተመልሰዋል፤ ማዳመጥ ባለመቻላቸው። በዚያው አልቀሩም ፤ ወደከተማዋ ዳግም በማቅናት ውሳኔያቸውን እንጂ ይቅርታን ካልጠበቀው ነዋሪዉ ፊት በመቅረብ "ይቅርታዬን ተቀበለኝ !" ያሉና፤ የዕድሜ-ፀጋን የተላበሱ የሮቤ ልጆች ዛሬም ድረስ ለሚያወጉት ክቡር ታሪክ የበቁ ናቸው።

የአርሲው ልጅ ፊታውራሪ መሀመድ ዓሊ ነዋሪውን በተጋፈጡ ችግሮች ጣልቃ በመግባትና በመሀከሉ ለተፈጠሩ አለመግባባቶች ከጎኑ ሆነው በመሸምገልና መፍትሄ በመሻት ይታወሳሉ። "የሮቤ አባት" ይሏቸዋል። የዘረጉት የሰላም እጅ ሳይታጠፍ፤ ያነገቡት የፍቅር ሰንደቅ ከትከሻቸው ሳይወረድ፤ እስከ ህልፈታቸው የዘለቁ ነበሩ። በጡረታ ዘመናቸው የህመም ቁራኛ ከሆኑበት መኖሪያ ቤታቸው በድጋፍ ተይዘው፤ ጊዜ ወለዱን የጎሳ ግጭት ለማብረድ ረዥም መንገድ ተጉዘዋል። ተፋላሚዎቹን ፊት ለፊት በመሞገትና ደም የሸተተውን ወገን "ጥቁር ውሻ ውለድ" ብለው በመርገም ከድርጊቱ እንዲታቀብ ድርሻቸውን ተወጥተው ወደ እማይቀርበት ማረፊያቸው በክብር ተሸኝተዋል።

ሁለቱም አዛውንት የቀዳማዊ ሃይለስላሴ ባለስልጣናት ነበሩ። ደጃች አባይ፤ በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት የጢቾ አውራጃ ገዥ ሲሆኑ፤ ፊታውራሪ መሀመድ በአውራጃዋ ካሉ ወረዳዎች አንዷ ለሆነችው ሮቤ ገዥ ነበሩ። እነዚህ የወቅቱ ባለስልጣናት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የችግሩ መንስዔም ሆነ መፍትሄ እራሳቸው መሆናቸውን በመገንዘብ፤ ግልፅነትና ሀላፊነት በተሞላበት መንፈስ ከሚያስተዳድሩት ህዝብ ጋር ሆነው የተጓዙበት ጠመዝማዛ መንገድና ፤ ስነልቦናውን በማጤን ወገናዊነታቸውን ያሳዩቡት ሥርዓት አጀብ የሚያስብልና በታሪካዊነቱና አርአያነቱ ሊዘከር የሚገባው ነው።


Fጭላሎ ተራራ
http://9000milesfromnormal.blogspot.com/2014/01/chilalo-

ደጃች አባይ በአንድ ወቅት አቅደው ሮቤዎች እንዲፈፅሙ የተወሰነው የመንገድ ስራ አፈፃፀም ክስተት በእርሳቸውና በነዋሪው መሀከል ላለው ያለመግባባት ዋና መንስዔ ነበር። የአባይ ካሣ ግዛት- ጢቾ አውራጃ - ለም ከሚባሉት የኢትዮጵያ ክልሎች አንዱ ብትሆንም፤ የመልክዓ ምድር አቀማመጧ ለልማቷ መሰረት የሆነውን መንገድ ለመዘርጋት አላደላትም። በተለይ የገዥው መቀመጫ የሆነችው ጢቾ ከተማ ከጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ ከሆነችው አሰላ ጋር አለመገናኘቷ ለደጃዝማቹ እረፍት የሰጠ ጉዳይ አልነበረም። በሁለቱ ከተሞች መሀከል ተጋርጦ የቆመውን የጭላሎ ተራራ (ጋላማን) ሰንጥቆ የሚገባ አውራ ጎዳና ለመዘርጋት ይወስናሉ። ዕቅዱንም ነድፈው፤ ለተግባራዊነቱ የከተማዋን ነዋሪና የወረዳውን ገበሬ ተነስ ብለውና ዶማና አካፋውን አሲይዘው አድካሚና እልህ አስጨራሽ የሆነውን የመንገድ ቁፋሮ አያይዘውታል። የመንገድ ዝርጋታው ሂደት በአውራጃው ስር ባሉ የወረዳ ከተሞችም እንዲዛመት እቅድ ነድፈው ለአፈፃፀሙ መመሪያ ያስተላልፋሉ።

ሮቤም እንደወረዳነቷ የመንገድ ስራው ዕቅድ ይደርሳታል። ድርሻዋ፤ ዋና ከተማዋን ጎረቤት ከሆነችውና ስሬ እየተባለች ከምትታወቅ የወረዳ ከተማ ጋር በማገናኘት በቀላሉ ወደ አሰላና ናዝሬት ከሚያዘልቀው አውራ ጎዳና ጋር ማያያዝ ነበር። በተለይ ቁርሱን ከቤቱ፤ ምሳውን ከናዝሬት ለማድረግ ሲመኝ ለነበረው ለሮቤ ከተማ ነጋዴ ዜናው የምስራች ያህል ነበር። ይሁን እንጂ፤ ደስታውን በቅጡ እንኳ ገልፆ ሳይጨርስ፤ ከደጃች አባይ ስለታቀደለት የመንገድ ስራ አፈፃፀም ያልጠበቀው መልዕክት ተከታትሎ ይደርሰዋል። " ለአቅመ-አዳም የደረሰ የከተማዋ ነዋሪ በነፍስ ወከፍ ዶማና አካፋውን አዘጋጅቶ ለዘመቻው እንዲዘጋጅ" የሚል ነበር። ከተሜው እንደአቅሙ ገንዘብ በማሰባሰብ ሙያተኛና ጉልበተኛ ቀጥሮ ለማሰራት እንጂ ፤ ንግዱን አቁሞና ከቤቱ ርቆ ወራት በሚያስቆጥረው የመንገድ ጠረጋ ድንጋይ ፈንቅሎ ለመካብ ፤ አፈር ለመቆለል ፤ የድልድይ እንጨት ተሸክሞ ለማንጠፍ አልተዘጋጅም። ለተበየነበት የስራ ድርሻ ያለውን ቅሬታ ለመልዕክተኞቹ ቢያሰማም ፤ " ከእርሳቸው ጋር ተነጋገሩ" የሚል ምላሽ ነበር ያገኘው።

ነዋሪው አቤቱታውን በጥሞና ለማስረዳት ብቃት አላቸው ያላቸውን ሽማግሌዎቹን በመሰየም ደጃች አባይ ከከተማው መጥተው በግንባር እንዲያናግሩት ቀነ-ቀጠሮ ያስይዛል። አባይም ቃላቸውን አክብረው በህዝቡ መሀከል ይገኛሉ። እንደተጠበቀው ተወካዮቹ ከፊታቸው በመቅረብ ነዋሪው በነፍስወከፍ ወጥቶ የመንገድ ስራውን ለማከናውን ያለበትንና

ሊገጥመው የሚችለውን ችግር በመግለፅ ላፈፃፀሙ አማራጭ የተባሉትን መንገዶች ይጠቁማሉ። ይህ የአዛውንቶቹ "ጉልበታችን በገንዘብ ይለወጥልን" ንግግር የደጃች አባይን ቀልብ ሊስብ አልበቃም። የነዋሪው ተማፅዕኖ ይበልጥኑ ትዕግስታቸውን በሚሚጠጡ፤ ብስጭታቸውን እንኳ በወጉ ሊቆጣጠሩት አልቻሉም። ከያዙት ስልጣን ጋር ያልመጠነ ዘለፋና የዛቻ ቃል በተወካዮቹ ላይ መሰንዘሩን ተያያዙት። አዛውንቱ ሁኔታውን ለማብረድና ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት ቢሞክሩም ፍቃደኝነታቸውን ሊያገኙ አልቻሉም። መደመጥ የተነፈገውና መሰደቡ ያበሳጨው የሮቤ ነዋሪ የተመካከረበት ይመስል ፤ አውራጃውን ገዥ ሳይሰናበት እተሰየሙበት ወንበር ላይ እንዳሉ ጥሏቸው ወደየመጣበት ነጎደ።

የከተሜው ስብሰባ ረግጦ የመውጣት ድርጊት ለደጃች አባይ ያልተለመደ፤ አስገራሚና አዕምሯቸው ሊቀበለው የቻለ አልነበረም። "እኔ አባይ ! መንገዱን ትግራይ ተሸክሜ ልሂድ አላልኩ! ዐይንህ ይገለጥ ባልኩ የሮቤ ህዝብ አዋርዶኝ ይሂድ!" በሚል ምሬታቸውን ለቅርብ ባለስልጣኖቻቸው ሲገልፁም ተደምጠው ነበር። በእርሳቸው እይታ የሮቤ ከተማ ነዋሪ ፤የጭላሎን ተራራ ሰንጥቀው አሰላ ለመግባት በጉልበትና በገንዘባቸው ትግሉን ከገጠሙት የጢቾ ከተማና የአካባቢው ወረዳ ገበሬዎች የተለዩ አልነበሩም። የግምጃ ቤት አስተዳደራቸው በተለይ የሮቤ ከተማን የንግድ ስፋትና በመስኩ የተሰማራው ነጋዴ ግለሰብ ያለውን የሀብት መጠን በእርግጠኝነት ለማወቅ የሚያስችል ልምዱም ሆነ ስርዓቱ ስላልነበረው ፤ የነዋሪው " በገንዘባችን እናግዝ " ጥያቄ ለእርሳቸው የመንገዱን ሥራ ከማጓተትና የስንፍና ምልክት ከመሆን ባለፈ ሌላ ትርጉም ሊሰጥ አልቻለም። በዕለተ-ስብሰባውም ከተሜውን ለማወቅ፤ አቅሙን ለመገምገምና ከተወካዮቹም ተጨማሪ ማብራሪያ ለመሻት ዝግጅቱም ሆነ ትዕግስቱ አልነበራቸውም።

ሮቤዎች በመሰረቱ "ስለነጋዴነታቸውና ከተሜነታቸው" ለማቅረብ የሞከሩት የመከራከሪያ ነጥብ ዕውነትነት ነበረው። ከተማቸው፤ ያን ጊዜ ፤ ከተቀሩት የአውራጃው ከተሞች በንግድ ማዕከልነቷ የገዘፈችና ባቀፈችው የብሄረ-ስብ ስብጥሯ ኢትዮጵያዊ ውክልናዋ በጉልህ የሚስተዋልባት ነበረች።ነዋሪው ባመዛኙ በንግዱ ስራ የኃለበተ፤ የበርካታ ቀላልና ከባድ የጭነት ማመላለሻ መኪኖች፤ የእህል መጋዘኖችና ንግድ መደብሮች ባለቤት ነበር።ይህ የከተማዋ ሞቅ ያለ የንግድ እንቅስቃሴ የነዋሪዋን ቁጥር ለማሳደግና የከተማዋን ልጆች ከተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ለመሳብ ልዩ ድርሻ ነበረው።ጉራጌው ፤ አርሲው፤ ሰላሌው ፤ መንዜው፤ ጎጃሜው፤ ጎንደሬው፤ ትግሬው ፤ ከምባታው፤ ሱማሌው፤ የየመኒው አረብ ሳይቀር በአንድ ማዕድ ተቋድሶባታል። ተዋልዶ ከብሮባታል ። ጉራግኛ፤ ኦሮምኛና አማርኛ የከተማዋ መግባቢያ ነበሩ። ሶስቱን አቀላጠፎ መናገር የነጋዴነቱ፤ ብሎም የሀብታምነቱ ጎዳና መስመር መቃናቱ፤ የኢኮኖሚያዊው እስትስስሩ መዳበር መልክቱ እንጂ ፤ የጎጠኝነቱ መለያው አልነበሩም። በከተሜው እምነት፤ ይህን በመሰለ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተገንብቶ የሚገኘውን ኑሮውንና

ሞቅ ያለ የንግድ እንቅስቃሴውን ላልተወሰኑ ወራት ዘግቶ፤ ልምዱና ሙያው ባልሆነው አድካሚ የመንገድ ስራ መሳተፍ ንግዱን ከማድከም ያለፈ ፋይዳ አላየበትም።

ሮቤዎች በዕለተ-ስብሰባው ያስተዋሉትን የደጃዝማቹን የብስጭትና እንቢተኝነት መንስዔ ከግምት ባለፈ በትክክል ለመረዳት የቻሉበት ሁኔታ ባይኖርም፤ ክስተቱ በረዥም ያስተዳደር ዘመናቸው የሚያውቋቸውን አውራጃ ገዥ እንደማይወክል በእርግጠኝነት የሚናገሩት ጉዳይ ነበር። በነዋሪው አገላለፅ ፤አባይ ካሣ በስመ-ጥር አርበኝነታቸው ፤ሰርተው በማሰራት አርአያነታቸው የሚታወቁ ነበሩ። ባንዳን በመጥላትና በስልጣን ባላጊን በመዋጋት ባህርያቸውም በእጅጉ የታወሳሉ። በአንድ ወቅት በጉቦኛነታቸው የሮቤ ከተማ ነዋሪ የተማረረባቸውና ከጠቅላይ ግዛቱ ዋና ገዥ ጋር ባላቸው ጥብቅ ትስስር አይደፈሬ እንደነበሩ የሚነገርላቸው አንድ የከተማዋ የመንግስት ሹም፤ ፍትህ በተነፈገ ግለሰብ ክስ ተመስርቶባቸው ደጃች አባይ ፊት እንዲቀርቡ መጥሪያ ትዕዛዝ ከአንዴም ሁለቴ ይላክላቸዋል። በአካል ቀርበው ክሱን ለመከላከል እንቢተኛ ይሆናሉ። ባለስልጣኑ በእርግጥም ከህግ በላይ መሆናቸውን የተገነዘቡት አውራጃው ገዥ በህግ ተገደው እንዲቀረቡ ትዕዛዝ የሰጣሉ። ሹሙ ለዚህኛውም ትዕዛዝ አልተበገሩም። ወደ ደጃች አባይ ካሣ የፍርድ መንበር ከመቅረብ ይልቅ በቀጥታ ወደ ጠቅላይ ግዛቱ ገዥ በማምራት፤ በቀጭን የስልክ ትዕዛዝ “ ክሱ የመንግስት ባለስልጣኑን ወርቃማ የስራ ጊዜ አባካኝ በመሆኑ እንዲዘጋ ” የሚል መልዕክት ለደጃች አባይ እንዲደርስ ያስደርጋሉ። ደጃች አባይ ከሣም “ለበላይ ባለስልጣኑ የበላይ አለው፤ ከህግ በላይ ግን እንኳን አገረ ገዥው ንጉሡም አይሆኑም ” በማለት የከተማዋ አመፀኛ የመንግስት ሹም በአውራጃ ግዛታቸው በማናቸውም የስልጣን እርከን እንዳያገለግሉ ፍርድ በመስጠት በቦታው በሮቤ ከተማ የሰፈነውን ጉቦኝነት የሚዋጋ ባለስልጣን እንደሾሙበት ዛሬም በህይወት ያሉ ይመሰክሩላቸዋል።



{ዳኝነት } education.francetv.fr

በእንዲህ መሰል ተግባራቸው ለሚያውቃቸው አባይ ካሣ ጀርባ ሰጥቶ ኑሮውን መቀጠሉ አግባብ ያለመሆኑን የተገነዘበው የሮቤ ህዝብ ዳግም ከፊታቸው በመቅረብ ጉዳዩን ለማሰማትና እሽታቸውን ለማግኘት አላንገራገረም፤ ጊዜም አላጠፋም ። ከሁሉም በላይ ነዋሪው ረግጦት በወጣው በዚያ ስብሰባ ሳቢያ ፤ ደጃዝማቹ ተደፈርኩ ብለው ሳንጃ አለማስመዘዛቸው፤ ማሰር፤ መቅጣት “ስልጣናቸው” ሆኖ “አምጡልኝ” ብለው ተወካዮቻቸውን አለማበታቸውና “ጥጋበኛ ህዝብ” ብለው በጅምላ አለመቅጣታቸው የነዋሪውን ከፍ ያለ አክብሮት አጎናፅፏቸዋል። በራሱ አነሳሽነትም ለጀመረው እርቀ-

ሰላም መግፋት ብርታቱን የሰጠ ሁኔታ ነበር። በጊዜው የወረዳው ገዥ የነበሩትን ፊታውራሪ መሀመድ ዓሊን ጭምር ያሳተፈ ስብሰባ በማካሄድና አንድ የሽማግሌዎች ቡድን በመሰየም፤ ከከተሙባት ጢቾ ከተማ ድረስ ሊያስማራ በቅቷል።

ፊታውራሪ የሮቤዎችን ኑሮ በመኖርና ስሜታቸውን በማንበብ አኳይ ከአውራጃው ገዥ የቀረቡና፤ የተፈጠረውን ልዩነት አጥብቦ ሰላም ለማስፈን ልዩ ሚና መጫወት የሚችሉ ነበሩ። ባዳማጭነታቸው፤ በቅን አገልግሎታቸው በእጅጉ ይታወቃሉ። በጡረታ ተገልለው እንኳ ለነዋሪው ደህንነት መጠበቅ ከመጨነቅና ከመስራት የታቀቡ አልነበሩም። ሀገሬው በልቡ ክቡር ቦታ ሰጥቶት በኩራት ከሚያወሳው ተግባራቸው መሀከል፤የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ግንባር የመሀል ሀገሩን በተቆጣጠረበት ወቅት በከተማዋና አካባቢዋ ባሉ ገበሬ መንደሮች ባልተለመደ ሁኔታ ከፋኛ አንዣቦ የነበረውን የኅሳ ጥላቻና ደም መፋሰስ ለማስቆም ያደረጉት አስተዋፅኦ አንዱ ሆኖ ይገኛል። አዛውንቱ መሀመድ ለአመታት በፍቅርና በሰላም የኖረው የሮቤ ከተማና የአካባቢው ነዋሪ በዘር ጥላቻ መታመሱን እንደሰሙ “የሮቤን ህዝብ ጥሩልኝ” ይላሉ። የህመም ቁራኛ ከሆኑበት አልጋቸው በድጋፍ ተይዘው ወደ ከተማዋ ዕምብርት በማምራት ተሰብስቦ ለጠበቃቸው ህዝብ ስሜት የሚነካ የሰላምና የፍቅር ጥሪ ያስተላልፋሉ። በማሳረጊያቸውም “ በአንድ ቤተክርስቲያን ፤ በአንድ መስጊድ አብረህ የፀለይክ፤ እስላም፤ ክርስቲያን፤ጉራጌ፤ አማራ ፤ ኦሮሞ እያልክ ደም መቃባትህን ከእንግዲህ ብትቀጥል “ጥቁር ውሻ ውለድ!” ብለው በማውገዝ፤ በወረዳዋ ያንዣበበው አመፅ ለሰላምና ለፍቅር እንዲንበረከክ አድርገዋል። ብዙም ሳይቆዩ ህመማቸው ፀንቶ፤ ህይወታቸው


{ቃልኪዳን ለሰላምና ፍቅር }
optimistworld.com

አለፈ። የወረዳው ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ የጀግና ቀብር ሥነ-ስርዓት አደረገላቸው ። እንደየብሄረሰቡ ወግና ባህል ጦሩን ከፍ አድርጎ ሰለቀላቸው። ከበሮውን እየደለቀ አሻም አለላቸው። ጠብመንጃውን ከፍ አድርጎ በሸለላ፤ በቀረርቶ አጀባቸው።ያስረከቡትን የመቻቻል ኑሮ ፤ሰላምና ፍቅር ለመጠበቅ ቃል ገብቶና እጅ ለእጅ ተያይዞ ወደ እማይቀርበት የዘላለም ማረፊያቸው አጅቦ በክብር ሸኛቸው።

እነኚህ ተከባሪ ወረዳ ገዥና የሮቤ ህዝብ መርቀው የሸኙት የሽምግልና ቡድንም እጅ-አመድ አፋሽ ሆኖ ከጢቾ ከተማ አልተመለሰም። የደጃች አባይ ካሣን የክብር አቀባበል ያገኘ ነበረ። የሮቤዎች አመፅ አባይ ካሣ አደብ እንዲገዙ፤ ጊዜ ወስደው ባፈፃፀም ሂደት የተከሰተን አለመግባባት ተወያይቶ፤ አምኖና አሳምኖ ለመፍታት የሚያስችል ግንዛቤ እንዲያገኙ የራሱን ድርሻ ተጫውቷል። የትግራዩ ልጅ- አባይ ካሣ - “ ህዝቡን አስቀይሜዋለሁ፤ ይቅርታዬን ይቀበለኝ፤ እንደፍላጎቱም በገንዘቡ ድጋፉን ይስጥ” የሚል ምላሽ እዚያው በግንባር ለተወካዮቹ ሊሰጡ በቅተዋል። በዚህም አላቆሙም። ወደ ሮቤ

ከተማ በማቅናትም ራሳቸውን ከነዋሪው ፊት ዝቅ አድርገው "ይቅርታዬን ተቀበለኝ !" ያሉና ላለመግባባቱ የማያዳግም ዕልባት የሰጡ የጊዜው ተከባሪ አውራጃ ገገር ነበሩ።

እዛሬ ላይ ሆኖ ወቅቱን ለመገምገምና ለመፍረድ ባይቃጣም፤ ባለስልጣናቱ ስህተትን በጊዜው አለማረም የድንቁርና የሀገር ጉዳት መግለጫ ባህርይ መሆኑን አበክረው ያስመዘገቡበት መድረክ ነበረ። የነዋሪው የወል አስተሳሰብ የልማቱ ዕድገት ነፀብራቅ፤ የህብረ-ብሄረሰቡ የስራ በህል ድምር ውጤት ነበር። የከተማው ጉራጌ ለአማራውና ኦሮሞው ፤ ኦሮሞው ለከምባታው፤ ለጉራጌውና አማራው …. ባጭሩ አንዱ ብሄረ-ሰብ ለሌላው ሙያውንና እውቀቱን የቸረበት ፤ አክብሮቱን ያጎለበተበት እንጂ ፤ አንድ ወጥ ብሄረ-ሰብ ክልሉን አጥሮ በፀጉረ-ልውጥነት ሌላውን የሀገር ልጅ የተጋፋበት ፤ በጥላቻ ስሜት ክቡር ህይወቱን ለማጠፋት ለፈረጁበት ወገኖች መድረኩን የሰጠበትና ፈር ለቆ የሄደበት ክስተት አልታየም። የገዥዎቹም ብቃት መለኪያ ዘርና ህይማኖታቸው ሳይሆን ፤ ያስተዳደር ልምዳቸው ፤ሚዛናዊ ፍርዳቸውና ችግሩን ለመቅረፍ አብረው ከነዋሪው ጋር መኳተናቸው ነበረ። ይህ ተግባራቸው በጡረታ ተገልለው እንኳ የህዝቡን ቀና አመላካከት ፤ ይቅር ባይነትና ፍቅር ሊያጎናፅፋቸው በቅቷል። አስተዳደር ፤ አደብ የገዛ አንደበትን የተላበሰና ሰላማዊ ትግልን ያካተተ መሆኑን አመልክተዋል። ለሀገር ልማት ሲባል በሚደረግ ውይይትና የሃሳብ ግጭት አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት፤ ካለም የሚከበሩበት ፤ የሚከባበሩበት መሆኑን አስተምረውን አልፈዋል። የደጃዝማቹም ሆነ የፊታውራሪው ያስተዳዳር ዘመናቸው ታሪክና የነዋሪው ማህበራዊ ህይወት፤ በዕድሜ ባለፀጋዎቹ የሮቤ ልጆች መናፈቁና በኩራት ዛሬ ድረስ በእጅጉ መወሳቱም አብይ መሰረቱ ይኸው ነበር።

ምንጭ፤ በህይወት ያሉ የአርሲ-ሮቤ ከተማ አዛውንቶች ፤